የትግራይ ከልል ከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሞተር ሳይክል፣ ቶታል ስቴሽን፣ ፕሮቨር ጃር የነዳጅ መለከያ፣የክብደት ማነፃፀርያ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ረቡዕ ሕዳር 24, 2012 (ከ 7 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: ታሕሳስ 9, 2012 8:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:በየሎቱ የተለያየ ነው
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:50
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ታሕሳስ 9, 2012 8:30 ጥዋት
- ምድብ: መለዋወጢ ኣቁሑት ተሸከርካርቲ/ ኮንስትራክሽን ማሽነሪን ኣቁሑትን/ ኤሌክትሮኒክስ መሳርሕታትን መለዋወጢን/ ናይ ምህንድስና ኣቁሑት/ ዕድጊት ሞተርሳይክል/

ጨረታዉ በጋዜጣ የወጣበት ቀን ህዳር 24/2012 ፡ ጨረታዉ የሚዘጋበት ቀን ፡ በ16ኛዉ ቀን ከሰዓት በሃላ በ 8:00 ሰዓት ጨረታዉ የሚከፈትበት ቀን ፡ በ16ኛዉ ቀን ከሰዓት በሃላ በ 8:30 ሰዓት

- ሎት-1 ሞተር ሳይክል
- ሎት- 2 ቶታል ስቴሽን
- ሎት -3 ፕሮቨር ጃር የነዳጅ መለከያ
- ሎት- 4 የክብደት ማነፃፀርያ

- በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ ንግድ ምዝገባ ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /ቲን ነምበር/ ማቅረብ የሚችሉ።
- በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡና ማቅረብ የሚችሉ።
- የመስከረም 2012 ዓ.ም ዲክለር ያረጉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
- ተጫራች የጨረታው ሰነድ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 16 ተከታታይ ቀናት ከትግራይ ከልል ከተማ ልማት ቢሮ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 59 የማይመለስ ብር 50.00 /አምሳ ብር/ በመከፈል መውሰድ ይችላሉ::
- ጨረታው የሚከፈተው በ16ኛው ቀን ከሰዓት በኋላ በ 8:00 ሰዓት ተዘግቶ በተመሳሳይ ቀን 8:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ትግራይ ከልል ከተማ ልማት ቢሮ ግዥና ንብረት ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 59 የሚከፈት ሲሆን ተጫራች
  ባለመቅረቡ የሚመለስ ሰነድ አለመኖሩን እየገለፀን 16ኛው ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል።
- ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ ለሞተር ሳይክል ብር 15,000/አስራ አምስት ሺህ ብር/ለቶታል ስቴሽን 100,000 መቶ ሺህ ብር ፕሮ ቨር/ጃር /የነዳጅ መለኪያ ብር 15,000 | አስራ አምስት ሺህ ብር / የክብደት መለኪያ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ በCPOማስያዝ ይኖርባቸዋል።
- ተጫራቾች ለመወዳደሪያ የሚያቀርቧቸው ሰነዶች ኦሪጅናልና ኮፒ ለየብቻ በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ አለባቸው።
- ተጫራቾች ሰነድ ላይ የተዘረዘሩትን ዕቃዎች እያንዳንዱን የተቀመጠ ዋጋ ከነቫቱ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።
- ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት ሰነድ ከስርዝ ድልዝ የፀዳና በእያንዳንዱ ገፅ ማህተምና ፊርማ መኖር አለበት። ሰነድ ጨረታ በሙሉ ም ሆነ በከፊል ማስቀረት ከጨረታ ውጪ ያደርጋል።
- ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር: 034-240-01-29 ወይም 03-44-40-89-73 ፋክስ ቁጥር 0344415859

አድራሻ : - የትግራይ ከልል ከተማ ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ መቐለ

የትግራይ ክልል ከተማ ልማት ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ